በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ገ/ኢ/1/2/65
Ref. No.
ቀን 28/08/2007
Date

**ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና በህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 40/2007 የሚያሻሽል መመሪያ ወጥቷል፡፡

ስለዚህ የመመሪያውን 2 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሱፊያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
<u>አዲስ አበባ</u>

Lettt.W/GT

ስልክ የፖ.ሣ.ቁ ፋክስ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 40/2007 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የወጣው መመሪያ ማሻሻያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ማሻሻያ

የመመሪያው አንቀጽ 3 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 3 ተክቷል፡-

"3. በዚህ መመሪያ መሠረት በፍራንኮቫሉታ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ሊገቡ የሚችሉት ከመመሪያው ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ 1 በተጠቀሱት ክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች ለሚገኙ ነዋሪዎች እንዲውሉ ወደአገር ለሚገቡ በሠንጠረዡ ለተዘረዘሩ ምግቦችና ባህላዊ አልባሳት ብቻ ነው።

## 3. ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ ከግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ______ ቀን 2007 ዓ.ም.

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ቃ/ክ/ፊ/5/934
Ref. No.

ቀን 14/1/2008
Date

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 40/2007 እንደገና ለማሻሻል የሚያስችል መመሪያ ወጥቷል::

ስለዚህ የመመሪያውን 2 ገጽ ፎቶ ኮፒ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከመስከረም 15 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

ሱፍያን አሕመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
<u>አዲስ አበባ</u>

Letter/WA/TA

## በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 40/2007

## ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለመፍቀድ የወጣውን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "በአንዳንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ የምግብ ሸቀጦች እና ባህላዊ አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ (በፍራንኮቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   ከመመሪያው ጋር ተያይዞ የሚገኘው ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 3፣5፣6 እና 7 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

| ተራ ቁ. | ክልሎች/ከተሞች | የተፈቀደላቸው ወረዳዎች | የተፈቀደ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | የምግብ አቅርቦት | ባህላዊ አልባሳት | |
| 3 | የቦረና ዞን | ሚኦ፣ ዲሎ፣ ጣኽስ፣ተልተሌ ወረዳ፣ በሚጋ ወረዳ መጋሎ ቀበሌ፣ አሬሮ፣ መልካ ሶዳ፣ ዱግዳ ዳዋ | ሩዝ፣ ፓስታ፣ መኮረኒ፣ ስኳር፣ ዘይት እና የስንዴ ዱቄት | | |
| 5 | በባሌ ዞን | ዳዋ ሠረር፣ ጎራ ዳሞሌ፣ ራይቱ፣ ሰዌና፣ ዳዋቅችን፣ መደወለቡ፣ ለገሂዳ፣ በርበሬ ወረዳዎች | .. .. | | |
| 6 | በጉጂ ዞን | ሊበን፣ ጉራዶላ፣ ጊርጃ፣ ሶባ ቦሩ፣ ነገሌ፣ ዋደራ ወረዳዎች | .. .. | | |
| 7 | በምስራቅ ሐረርጌ ዞን | ጭናክሰን፣ ጉርሱም፣ ጃርሶ፣ ባቢሌ፣ ሚደጋ ቶላ፣ ማር፣ ጎዶ አዶ፣ ቁምቢ፣ ጎሮጉቱ ወረዳዎች | .. .. | | |

## 3. ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ ከመስከረም 15 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ______ ቀን 2008 ዓ.ም.

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

Memery/Ws/TA